በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን።

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 7

## መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon4@gmail.com

*ቦታ፡-* ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

ሚያዝያ ፫ ቀን ፳፻፬ ዓ.ም.

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 7

## ጸጥተኛነት

- ጸጥተኛነት አንዳንድ ጊዜ ደካማነት ሆኖ በተሳሳተ መንገድ ሲቆጠር እናያለን፡፡
- ጸጥተኛ ሰው፡-
    - መጨቃጨቅ  አይወድም አመለካከቱን ወይም አቋሙንም በኃይል ወይም በቁጣ ሊገልጥ አይወድም፡፡
    - ሁሉን በጸጋ እየተቀበለ እግዚአብሔርን ያመሰግናል፣ የነገሮችን በጎ ጎናቸውን ይመለከታል፣ ዘወትር ለመታዘዝና ለማገልገል ዝግጁ ነው፣ ሌሎችን ያበረታታል፣ ያደንቃል፣ ሌሎችን ለማስደሰት የበቃና የነቃ ሕይወት አለው፡፡
    - ሕይወትን ለመጋራት ብቃት ያለው/ያላት የሕይወት አጋር ነው/ናት፡፡
    - ጸጥተኛ ሚስት በባልዋ ላይ ፈጽሞ ጫና አታበዛበትም፡፡
    - ጸጥተኛ ባልም ሚስቱ በምታደርገውም ሆነ ባለደረገችውም ጥረት ደስተኛ ነው፡፡
- ጌታችን በመዋዕለ *ሥጋዌው ‹‹ከእኔም ተማሩ፥ እኔ የዋህ በልቤም ትሑት ነኝና፥ ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ››* *ማቴ 11፡29፡፡* በማለት በተግባር ያሳየንም ሕይወት ይህ ነው፡፡
- ጸጥተኛ ክርስቲያን ከራሱ ይልቅ የሌሎችን መሻት ማስቀደምን ከጌታችን ይማራል፡፡

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 7

## ጸጥተኛነት

- ጸጥተኛነት ሌሎች በጎ ምግባራትን (መንፈሳዊ ፍሬዎች) የምታስገኝ፣ ሰላምና ደስታም የምታላብስ የምግባራት እናት ናት።
- ጸጥተኛነት ትዕግሥትን፣ ጽንዓትን፣ ትሕትናን፣ የልብ የዋሕነትን፣ ፍቅርንና ስምምነትን የምታስገኝ የበጎነት መገኛ ናት።
- ጸጥተኛነት ትሕትና የመላበት ልብ መገለጫ ናት። አንዳንድ ሰዎች በተፈጥሮአቸው ቀና ናቸው፤ በዚህም የተነሳ ጸጥተኛነት የሕይወታቸው ምልክት ሆና ትገኛለች።
- ይሁን እንጂ ጸጥተኛነትን ገንዘብ ለማድረግ በክርስትናችን ጠንክሮ መሥራት ይጠበቅብናል።
- ጌታችን ይህን ሕይወት ይሰጠን ዘንድ ዘወትር በጸሎታችን ብንጠይቀው እርሱም የጸጥተኛነት ባለቤት ያደርገናል።

## ይህን ሕይወትን ለመላበስ እንችል ዘንድ የሚከተሉትን ምክሮች እንጠቀምባቸው፦

1. ማመስገን

- ዘወትር እግዚአብሔርን ማመስገንን እንሰልጥንበት (እንማር)። በየዕለቱ ጸሎታችን ‹‹ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ አመሰግንሃለሁ›› ማለትን እንደጋግመው።
- የትዳር አጋራችን ለእኛም ሆነ፣ ለልጆቻችን እንዲሁም ለማንኛውም ሰው የምታደርገውን ማንኛውንም ነገር ማድነቅን እንሰልጥንበት (እንማር)።

**ጸጥተኛነት** <u>**የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 7**</u>

**ይህን ሕይወትን ለመላበስ እንችል ዘንድ የሚከተሉትን ምክሮች እንጠቀምባቸው፡-**

1. **ማመስገን**

- አድናቆታችንንም ጥቂት የምስጋና ቃላቶችንና ስጦታዎችን ለምሳሌ የሞባይል መልዕክቶችን ወይም አበቦችን በመስጠት እንግለጽ፡፡ ‹‹በሁሉ አመስግኑ፤ ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ በክርስቶስ ኢየሱስ ወደ እናንተ ነውና፡፡›› *<u>ቀዳ ተሰ 5፡18፡፡</u>*

2. **ፈገግታን መላበስ**

- ፈገግታ በዙሪያችን ለሚገኙ ሰዎች ሁሉ ልዩ ስጦታ እንደሆነ እንቁጠር፡፡
- ስለዚህም ነገር በችግር ውስጥ ብንሆንም እንኳ ከፊታችን ደግነት ያለበት ፈገግታ እንዲነበብ እናድርግ፡፡ ‹‹እነርሱ ባልታመኑ ጊዜ ሳቅሁላቸው የፊቴንም ብርሃን አላወረዱም፡፡›› *<u>ኢዮ 29፡24፡፡</u>*
- ፈገግታ ያለው ፊት (ገጽ) ሁልጊዜ ያስደስታል፣ ያበረታታል፣ ያጠነክራል፡፡

3. **ለቁጣ መዘግየት**

- በዙሪያችን ራሳችንንም ሆነ ሌላውን የሚያስቆጣ ነገር ሲገጥም ራሳችንን በመቆጣጠር እንጸልይ፡፡ ለራሳችንም እየደጋገምን ‹‹እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ - አቤቱ ክርስቶስ ሆይ ማረን፣ አቤቱ ጌታችን ሆይ ርዳን ፣ ጥበብን ስጠን፣ ስለዚህም እናመሰግንሃለን›› እንበል፡፡

ጸጥተኛነት

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 7

**ይህን ሕይወትን ለመላበስ እንችል ዘንድ የሚከተሉትን ምክሮች እንጠቀምባቸው፡-**

## 3. ለቁጣ መዘግየት

- ‹‹ተወዳጆች ሆይ፥ ራሳችሁ አትበቀሉ፥ ለቍጣው ፈንታ ስጡ እንጂ፤ በቀል የእኔ ነው፥ እኔ ብድራቱን እመልሳለሁ ይላል ጌታ ተብሎ ተጽፎአልና።›› *ሮሜ 12፡19* ‹‹በቁጣችሁ ላይ ፀሐይ አይግባ፥ ለዲያብሎስም ፈንታ አትስጡት… መራርነትና ንዴት ቁጣም ጩኸትም መሳደብም ሁሉ ከክፋት ሁሉ ጋር ከእናንተ ዘንድ ይወገድ።›› *ኤፌ 4፡27-31።*
- ባስቆጣን ነገር ላይ ፈጣን ምላሽ ወይም አስተያየት እንድንሰጥ ስንጠየቅ ከመመለስ እንቆጠብ።
- ምላሽ ከመስጠታችንም በፊት በቂ ጊዜ ለራሳችን እንስጥ፣ ጌታችንም ጥበብና ትዕግሥትን ይሰጠን ዘንድ እንጠይቀው። ‹‹ስለዚህ፥ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፥ ሰው ሁሉ ለመስማት የፈጠነ ለመናገርም የዘገየ ለቍጣም የዘገየ ይሁን›› *ያዕ 1፡19።*

## 4. ማማረርን (ምሬትን) ከእኛ እናርቅ

- ዘወትር የሚያማርሩ ሰዎች ሁለት ዓይነት ናቸው። አንደኞቹ ነገርን ሁሉ አጨልመው የሚመለከቱ ናቸው፤ ሌሎቹ ደግሞ ሁሉ ጊዜ ነገሮች ፍጹም ሆነው እንዲገኙ የሚጠብቁ ናቸው።

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 7

**ጸጥተኛነት**

**ይህን ሕይወትን ለመላበስ እንችል ዘንድ የሚከተሉትን ምክሮች እንጠቀምባቸው፡-**

**4. ማማረርን ከእኛ ማራቅ**

- ‹‹ምሬት ሞላብኝ በእሬትም አጠገበኝ፡፡›› ***ሰቆ ኤር 3፡15፡፡*** ‹‹ዛሬ ድምፁን ብትሰሙት፥ አባቶቻችሁ እኔን የፈተኑበት የመረመሩበትም አርባ ዓመትም ሥራዬን ያዩበት በምድረ በዳ በፈተና ቀን በማስመረር እንደ ሆነ፥ ልባችሁን እልከኛ አታድርጉ፡፡ ›› ***ዕብ 3፡8-9፡፡***
- ነገርን ሁልጊዜ አጨልመው የሚመለከቱ ሰዎች በሕይወታቸው የሚከሰተውን ነገር በበጎ መልኩ መመልከትን መማር (መሰልጠን) አለባቸው፡፡
- እነዚህ ነገርን ሁልጊዜ አጨልመው የሚመለከቱ ሰዎች እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ስለገባልን ታላቅ ቃልኪዳን ማስታወስ ያስፈልጋቸዋል፡፡ ስለቃልኪዳኑ የሚናገሩ ኃይለ ቃሎችን በመያዝ መመላለስ ይኖርባቸዋል፡፡ ከነዚህም ‹‹እግዚአብሔርንም ለሚወዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን፡፡›› ***ሮሜ 8፡28፡፡*** አንዱ ነው፡፡
- ነገር ሁሉ ፍጹም ሆኖ እንዲቀርብ የሚጠብቁ ደግሞ ዘወትር ዓይኖቻቸው በስህተቶችና በጥፋቶች ላይ የተተከሉ ናቸው፤ ስለዚህ እንደዚህ ያሉት ደግሞ ትዕግሥት (መቻቻል) እንዲበዛላቸው በራሳቸው ላይ ክርስቲያናዊ ሥራን መሥራት ይጠበቅባቸዋል፡፡

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ... - ክፍል 7

**ጸጥተኛነት**

**ይህን ሕይወትን ለመላበስ እንችል ዘንድ የሚከተሉትን ምክሮች እንጠቀምባቸው፡-**

## 4. ማማረርን ከእኛ ማራቅ

- ንስሐ ስንገባ ጌታችን የተወላቸውንና የረሳላቸውን ኃጢአታውንና ስህተታቸውን ለራሳቸው ማስታወስ ይጠበቅባቸዋል፡፡
- ስህተት ሠርተው ከእግዚአብሔርም ሆነ ከሰው ይቅርታን የፈለጉበትን ጊዜ በፊታቸው ማስቀመጥ ወይም ማስታወስ ይኖርባቸዋል፡፡

## 5. ጭቅጭቅንና ንትርክን ማስወገድ

- በተፈጥሮአችን ጭቅጭቅና ንትርክ የምንወድ ከሆንን ክርስቲያኖች ወደበርካታ ጭቅጭቆችና ንትርኮች ከመግባት ራሳችንን ልንጠብቅ ያስፈልገናል፡፡ ይልቁንም ያሰብነውን በኃይል እንድንገልጽ፣ እንድንቆጣ፣ ወደክስና ማውገዝ እንድንገባና መጥፎ ቃላት እንድንጠቀም ከሚያደርጉን ሁኔታዎች መሸሽ ይገባል፡፡
- ወደ ጭቅጭቅና ንትርክ ከመግባታችን በፊት ወደ ነገሩ መግባታችን ወይም ከነገሩ የመራቃችን አስፈላጊነቱ እንዲታየን፡ ጥበብና ሰጥቶ መንገዱንም ይመራን ዘንድ አጭር ጸሎት ወደ አምላካችን እግዚአብሔር እንጸልይ፡፡

# <u>የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 7</u>

**ጸጥተኛነት**

**ይህን ሕይወትን ለመላበስ እንችል ዘንድ የሚከተሉትን ምክሮች እንጠቀምባቸው፡-**

**5. ጭቅጭቅንና ንትርክን ማስወገድ**

- ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በጸሎት ስንጠይቀው የልባችንን መሻት እንደሚሰጠን ፈጽመን አንጠራጠር፡፡
- አስፈላጊ ሆኖ ወደ ነገሩ ከገባን በጩኸት ከመናገር እንቆጠብ፣ የዋህነት ያለበትን ፈገግታ ተላብሰን እንገኝ፡ የሌሎች አስተሳሰብ ከእኛ የተለየ ቢሆንም እናድንቅላቸው፡፡
- ራሳችንን ከሌላው ጫማ ሥር እናድርግ፡ በተቻለንም መጠን ሌሎችን እንረዳቸው፣ የምንለውንም በኩራትና በድፍረት ሳይሆን በፍጹም ትሕትና ሆነን እንግለጽ፡፡
- ልዩነታችንም ከተገለጸው ሐሳብ ጋር እንጂ ከሚገልጸው ሰው ጋር እንዳልሆነ እንረዳ፤ ይህም እንድናከብረው/እንድናከብራት ያለበትን/ያለችበትን ሁኔታ እንድንገነዘብ ያደርገናልና፡፡ ‹‹እንግዲህ ወንዶች በስፍራ ሁሉ አለ ቍጣና አለ ክፉ አሳብ የተቀደሱትን እጆች እያነሱ እንዲጸልዩ እፈቅዳለሁ፡፡›› <u>*ቀዳ ጢሞ 2፡8፡፡*</u>

# <u>የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 7</u>

## መጨረሻ በሌለው ፍቅር መዋደድ

- ‹‹ፍቅር ለዘወትር አይወድቅም፡፡›› ***<u>ቀዳ ቆሮ 13፡8፡፡</u>***
- በክርስቶስ የሆነች ትዳር እስከሞት ሳይለያዩ አብረው የሚኖሩባት በኋላም መንግሥተ ሰማያትን የሚወርሱባት ናት፡፡
- ይህም ፍቅር ተጋቢዎቹ የጋብቻቸው ምስጢር በተፈጸመበት ዕለት በተቀበሉት ቅዱስ ቁርባን ተጀምሮ እስከመጨረሻው አብሮአቸው ይቀጥላል፡፡ ‹‹እናንተም፡፡ ስለ ምንድር ነው? ብላችኋል፡፡ ሚስትህ ባልንጀራህና የቃል ኪዳንህ ሚስት ሆና ሳለች እርስዋን አታልለሃታልና እግዚአብሔር በአንተና በልጅነት ሚስትህ መካከል ምስክር ስለ ሆነ ነው፡፡›› ***<u>ሚል 2፡14፡፡</u>***
- ተጋቢዎች በተጋቡበት ዕለት እስከሞት ድረስ ላይለያዩ ቃል ይገባሉ፣ ይህም መልካም ጊዜ ተጋቢዎቹ ‹‹ እኔ የአንተ/የአንቺ ነኝ፡ ልቤ ወደ ሌላ ሰው እንዲሄድ ፈጽሞ አልፈቅድለትም፣ ከአንተ/ከአንቺ በቀር ማንኛውም ሰው የልቤ ቅርቡ እንዲሆን አልፈቅድም፣ በሕይወትም ከአንተ/ከአንቺ በቀር ፈጽሜ ደስ አልሰኝም የሚሉበት የተቀደሰ ዕለትና ሰዓት ነው፡፡
- ይህም ክርስቲያናዊ አስተሳሰብና ፍጹም መሥዋዕትነት ለኀልውናችንና ለደስታችን ቁልፍ ነው፡፡

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 7

## መጨረሻ በሌለው ፍቅር መዋደድ

- ተጋቢዎቹ ያደረጉት ይህ ቃል ኪዳን እግዚአብሔርና ሰው እንሚያደርጉት ቃልኪዳን ያለ ነው፡፡ ‹‹ቃል ኪዳኔ ከእርሱ ጋር የሕይወትና የሰላም ቃል ኪዳን ነበረ ይፈራ ዘንድም እነርሱን ሰጠሁት እርሱም ፈራኝ፥ ከስሜም የተነሣ ደነገጠ፡፡›› *ሚል 2፡5፡፡*
- ‹‹ባናምነው፥ እርሱ የታመነ ሆኖ ይኖራል፤ ራሱን ሊክድ አይችልምና፡፡›› *ሳል ጢሞ 2፡13፡፡* እንደተባለው እግዚአብሔር ዘወትር ቃልኪዳኑን የሚጠብቅ አምላክ ነው፡፡
- ሰው ግን ቃል ኪዳኑን መጠበቅ አልቻለም፡፡ ‹‹ከግብጽ አገር አወጣቸው ዘንድ እጃቸውን በያዝሁበት ቀን ከአባቶቻቸው ጋር እንደ ገባሁት ያለ ቃል ኪዳን አይደለም እነርሱ በኪዳኔ አልጸኑምና፥ እኔም ቸል አልኋቸው፥ ይላል እግዚአብሔር፡፡›› *ሔር 31፡32፡፡*
- እግዚአብሔር ግን ሰው ቃል ኪዳኑን መልሶ ይጠብቅ ዘንድ በርካታ ዕድሎችን ይሰጠዋል አሁንም እየሰጠው ይገኛል፡፡
- ከእግዚአብሔር የተለየ ትዳር በስሜትና (ፍትወታት እኩያትና) ቁሳዊ ነገር ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ በርካታ ትዳሮች መቀጠል አቅቶአቸው የሚፈርሱትም ለዚሁ ነው፡፡
- ስሜታዊ ቃልኪዳንና ሥጋዊ ፍላጎቶች የገዙት የትዳር ሕይወት ማንኛውም ትዳር የሚያልፍበትን ፈተና አሸንፎ ማለፍ ወይም መሻገር አይችልም፡፡

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 7

## መጨረሻ በሌለው ፍቅር መዋደድ

- በክርስቶስ በሆነ መጨረሻ በሌለው ፍቅር የታተመ ትዳር ግን ተጋቢዎቹ አስቸጋሪውን ፈተና የሚያልፉበት፣ ማንኛውንም መከራ የሚሻገሩበትና ሳይለያዩም የሚኖሩበት ነው፡፡
- ቃል ኪዳኑም ‹‹በክርስቶስ ያንተ/ያንቺ ነኝ!›› የሚል ነው፡፡ ይህም ማለት ዕረፍታችንን፣ ፍላጎታችንን፣ ምኞታችንን፣ መላ ሕይወታችንን ለሕይወት አጋራችን በክርስቶስ መሥዋዕት ለማድረግ መዘጋጀት ማለት ነው፡፡
- በክርስቶስ ለትዳር/ከትዳር አጋራችን ጋር እስከ መጨረሻ ለመኖር የሚያስችል ጥርጣሬ ካለን ለጋብቻው ፈጽመን ከመቸኮል እንቆጠብ፡፡
- ‹‹ተስለህ የማትፈጽም ብትሆን ባትሳል ይሻላል፡፡ሥጋህን በኃጢአት እንዳያስተው ለአፍህ አርነት አትስጥ፥ በመልአክም ፊት፡፡ ስሕተት ነበረ አትበል እግዚአብሔር በቃልህ ይቈጣ ዘንድ የእጅህንም ሥራ ያጠፋ ዘንድ ስለምን ትሻለህ?ብዙ ሕልም ባለበት ዘንድ፥ እንዲሁም ደግሞ ብዙ ቃል ባለበት ስፍራ በዚያ ብዙ ከንቱ ነገር አለ አንተ ግን እግዚአብሔርን ፍራ፡፡›› *መክ 5፡5-6፡፡* እንደተባለ ፍጻሜ በሌለው ፍቅር ያትመን ዘንድ ትዳራችንን እግዚአብሔርን መፍራት ያለቤት እናድርገው፡፡

# ይቆየን።

For your queries or questions E-mail:
kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :
www.zeorthodox.org